የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፵፩
አዲስ አበባ ግንቦት ፳፰ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

23rd Year No. 41
ADDIS ABABA, 5th June, 2017

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፰/፪ሺ፱ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስትና በኩዌት መንግስት መካከል በግብርና ዘርፍ ትብብር ለማድረግ የተፈረመውን ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ…………………………………………ገፅ ፱ሺ፮፻፶፫

## CONTENT

PROCLAMATION NO.1008 /2017

Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the State of Kuwait on Agriculture Cooperation Ratification Proclamation ………………………………………page 9653

### አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፰/፪ሺ፱

### በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስትና በኩዌት መንግስት መካከል በግብርና ዘርፍ ትብብር ለማድረግ የተደረገውን ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስትና በኩዌት መንግስት መካከል በግብርና ዘርፍ ትብብር ለማድረግ ሐምሌ ፲፬ ቀን ፪ሺ፩ ዓም በአዲስ አበባ ስምምነት የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ግንቦት ፲፭ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀፅ ፶፭ (፩)እና (፲፪) መሰረት የሚከተለው ታውጇል:-

### PROCLAMATION NO.1008 /2017

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUPBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF THE STATE OF KUWAIT AGRICULTURE COOPERATION

**WHERE AS,** the Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the State of Kuwait on Agriculture Cooperation was signed in Addis Ababa on the 21st day of July 2009;

**WHERE AS,** the House of the Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said agreement at its session held on the 23rd day of May 2017,

**NOW THEREFORE,** in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

፩. <u>**አጭር ርዕስ**</u>

ይህ አዋጅ "በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በኩዌት መንግስት መካከል በግብርና ዘርፍ ትብብር ለማድረግ የተፈረመውን ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፰/፪ሺ፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. <u>**የስምምነቱ መፅደቅ**</u>

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በኩዌት መንግስት መካከል በግብርና ዘርፍ ትብብር ለማድረግ ሐምሌ ፲፬ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመው ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

፫. <u>**አስፈፃሚ አካል**</u>

የእርሻና የተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር እና የእንስሳትና ዓሳ ሀብት ሚኒስቴር ከሚመለከታቸው ሌሎች አካላት ጋር በመተባበር ይህን ስምምነት እንዲያስፈፅሙ በዚህ አዋጅ ስልጣን ተሰጥቷቸዋል፡፡

፬. <u>**አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት ፳፰ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**



**1. <u>Short Title</u>**

This proclamation may be cited as the "Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the State of Kuwait on Agriculture Cooperation Ratification Proclamation No. 1008/2017".

**2. <u>Ratification of the Agreement</u>**

The Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the State of Kuwait on Agriculture Cooperation signed on the 21st day of July 2009 is hereby ratified.

**3. <u>Implementing Organ</u>**

The Ministry of Agriculture and Natural Resources and Ministry of Livestock and Fisheries in collaboration with the other concerned bodies are hereby empowered to implement this Agreement.

**4. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 5th day of June,2017**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**